ጨረቃን ባያችሁ ጊዜ ፁሙ! ባያችሁት ጊዜ ፆም ፍቱ! ከተጋረደባችሁ ደሞ ልኩን ገምቱለት።

ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህን መልክተኛ
(ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "ጨረቃን ባያችሁ ጊዜ ፁሙ! ባያችሁት ጊዜ ፆም ፍቱ! ከተጋረደባችሁ ደሞ ልኩን ገምቱለት።"» [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የረመዿን ወር መግቢያና መውጫን ምልክት ገለፁ። እንዲህ አሉ: የረመዿንን ጨረቃ ያያችሁ ጊዜ ፁሙ። በናንተና በጨረቃው መካከል ደመና ከገባና ከጋረዳችሁ ደሞ የሸዕባንን ወር ሰላሳ አድርጋችሁ ቁጠሩ። የሸዋልን ጨረቃ ያያችሁ ጊዜ ፆም ፍቱ። በናንተና በጨረቃው መካከል ደመና ከገባና ከጋረዳችሁ የረመዿንን ወር ሰላሳ አድርጋችሁ ቁጠሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4549